# ኪ ዳ ና ች ን
# KIDANACH'N

ልዩ ዕትም መስከረም ፩ ቀን፥ ፳፻፲፱ (፪ሺ፲፱) ዓመተ ምሕረት
Special Edition Meskerem 1, 2019 A.D
(September 11, 2026 G.C)

**ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መኾኗን፥
ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያትም፡ የቅዱሱ ኪዳን ሕዝብ መኾናቸውን ለማስረዳትና
የኢትዮጵያ እና የኢትዮጵያ ልጆች የኾነውንም ኹሉ፡ ለመጠበቅ፥ ለማሳወቅም፡
በ"ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት" እየተዘጋጀ የሚወጣ ዕትም።**

**Published by "Ethiopia: The Kingdom of God"
to reveal the Divine Truth about Ethiopia's entity as the Kingdom of God
and Ethiopians' identity as the People of the Holy Covenant with God;
and so, to safeguard and promote all that pertains to Ethiopia and Ethiopians.**

# የ፪ሺ፲፱ (፳፻፲፱) ዓመተ ምሕረት፡ ቀን መቍጠሪያ
## 2019 (2026-2027 Gregorian) Calendar

**አዘጋጅ፡-ንቡረ እድ፡ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ ዓባይነሽ።**



ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ
እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ
ካህኑ ለዓለም፡ በከመ ሢመቱ ለመልከ-ጼዴቅ ኢትዮጵያዊ
ንጉሠ ጽዮን፥ ወንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ
የይሁዳው ነገድ አንበሳ፡ ድል ነሣ!
እርሱም፡ በኢትዮጵያዊው መልከ-ጼዴቅ፡ የአጼነት ሹመት ሥርዓት፡
የጽዮን ንጉሥ፥ የመላዋ ኢትዮጵያም፡ የንጉሦችና የንግሥቶች ንጉሥ ኾኖ፡
በዘለዓለማዊው ክህነት የሚኖረው፡
እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ ነው።
The Triumphant Lion of the Tribe of Judah
God The Son, Jesus Christ
Eternal Priest in the Order of Melke-Zedeq the Ethiopian
King of Zion and King of Kings of Ethiopia

ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር
እግዚአብሔር እም፡ ድንግል ማርያም
እሙ ለመሲሕነ፥ ወእምነ ዘዚአነ
ንግሥተ ጽዮን፥ ወንግሥተ ነገሥታት ዘኢትዮጵያ
እጆቿን፥ ወደእግዚአብሔር አድርሳ የምትኖረው ኢትዮጵያ፤
የመሲሓችን እናትና የእኛም እናት፤
የጽዮን ንግሥት፥ የመላዋ ኢትዮጵያም
የንጉሦችና የንግሥቶች ንግሥት፡
እግዚአብሔር እም፥ ድንግል ማርያም ናት።
Ethiopia Reaches out Her Hands to God
Goddess The Mother: Virgin Mary
Mother of Our Messiah; Our Holy Mother
Queen of Sovereigns of Zion and Ethiopia

## ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት

# ልዑል እግዚአብሔር፡

## ከዘመነ ማርቆስ ፡ ወደዘመነ ሉቃስ አሸጋግሮ፡

**የኢትዮጵያን የነጻነት ህልውና በዓላችንን፡ ፯ሺ፭፻፲፱ኛ ዓመት፥**
**እና**
**የእግዚአብሔር እም፡ ድንግል ማርያምን፡ ፪ሺ፴፭ኛ ዓመት፥**
**የእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕን፡ ፪ሺ፲፱ኛ ዓመት፡**
**የትስብእት ልደታት በዓሎቻችንን፡ ለማክበር ለበቃንበት፡**
**ለዐዲሱ፡ የ፪ሺ፲፱ (፳፻፲፱) ዓመተ ምሕረት፡**
**እንኳን አደረሰን!**

\+ + +

# ስለቀን መቁጠሪያው መግለጫ።

፩ኛ፡- ይህ የቀን መቍጠሪያ የተዘጋጀው፡"**ኢትዮጵያ፡የዓለሙ መፋረጃ!**" በሚለው፡በ፲፱፻፺፫ ዓ.ም፣ ፳፻፱ ዓ.ም. እና ፳፻፲ ዓ. ም. በታተመው መጽሓፍ ውስጥ የተገለጹትንና አግባብነት ያላቸውን ሓተታዎች መሠረት በማድረግ ነው።

፪ኛ፡- "**በዘንዜከር**" በተባለው፡ የየዕለቱ የጸሎት መግቢያ፡ ለመዓልቱና ለሌሊቱ ቅመራ፡ መነሻ ኾኖ፡ ከሌሎቹ ቍጥሮች ጋር የሚደመረው **የ፳፻፲፱ቱ (የዕሥራ ምእት ዐሥርቱ ወተስዐቱ) [የ፪ሺ፲፱ኛው] ዓመተ ምሕረት፡ ዓበቅቴው፡ ፳፫ [ኻያ ሦስት]፥ መጥቅዑ፡ ፯ [ሰባት]** ኾኗል።

፫ኛ፡- በቀን መቍጠሪያው ሠንጠረዥ ውስጥ፡ በስም ብቻ የተጠቀሱት፡ ቅዱሳንና ቅዱሳት ነቢያትና ሐዋርያት፥ ጻድቃንና ሰማዕታት፡ ሌላ መግለጫ ካልተሰጠ በቀር፡ **ዕረፍታቸውን፥ የአኀዞቹ** [የቍጥሮቹ] እና የሣጥኖቹ የተለያዩ ቀለማት ደግሞ፡ ከዚህ የሚከተሉትን አብነቶች ያመለክታሉ፡-

ሀ. ቀዩ፡- **ዕለተ-ሰንበትን** *["ቅዳሜ" ስትባል የኖረችውን]*፥
**ዕለተ-ሰንበት ዝልፍትን** [በ"እሑድ" የቀጠለችውን "ዘለዓለማዊቷን ሰንበት" (ዝልፍት)]፥
ዓበይት በዓላትንና ተከታታዮቹን የፍስክ ዕለታትና ሳምንታት፣

በ. አረንጓዴው፡- ንኡሳን በዓላትን፣

ገ. ሰማያዊው፡- የአጽዋማት ቀኖችንና ሳምንቶችን፣

ደ. ወርቅማው፡- ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ በባዕዳን የማሰነውንና፡ሕያው ቅርስ ኾኖ የኖረውን፡የቅዱሱ ኪዳን የቀን አቆጣጠር ሥርዓቷን ይኸውም፣አጽዋማቷንና በዓላቷን፡ወደጥንተ ኢትዮጵያነቱ የመለሰች መኾኑን፡የሚያሳዩ ናቸው።

፬ኛ፡- **መስከረም ፩ ቀን፡-**

❖ምናልባት፡ በእየራሳችን ድክመትና ስሕተት፥ ጕድለትና ጥፋት፡ ሥጋዊና ነፍሳዊ፥ መንፈሳዊም ኹለንተናችንን፡ ያሳደፍንበትና ያበላሸንበት፥ ያሰነካከልንበትና ያስረጀንበት፡ አካላዊና ባሕርያዊ የኾነ፡ የአምልኮ ምንዝርና ግብር ቢኖር፡ ያን ኹሉ፡ የርኵሰትና የልክስክስነት ግብስብስና ዝባዝንኬ፡ **በእውነተኛ ንስሓ፡** ፈጽመን፡ ከሰውነታችን በማስወገድ፡ ወዲያ አውጥተንና አሽቀንጥረን ጥለን፣ ኹለንተናችንን፡ በመንፈስ ቅዱስ ጸጋዎች አንጽተን ያደስንባት፣

❖ከዚህም ጋር፡ **ቅዱስ ቊርባናችን በኾነው፡ በሥጋ ወደሙ፡** ኹለንተናችንን ቀድሰን፡ ሥጋችንንና ነፍሳችንን፥ መንፈሳችንንም፡ ለእግዝእተብሔር እም ድንግል ማርያም እና ለልጇ ለወዳጇ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ የልደታት በዓላችን ክብር ያበቃንባት፣

❖ሰላማችንን ያስገኘልን፡ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ ድኅነትን [መዳንን] ካስገኘችልን፡ ከእግዝእተብሔር እም ድንግል ማርያም በመወለዱ፡ **በቅዱሱ ኪዳን** የተጐናጸፍነውንና የተቀዳጀነውን፡ ዘለዓለማዊዉን የምሕረት ዘመን፡ የክብር ልብስና የሕይወት አክሊል፡ እንደዐዲስ ተሿሚና ተሸላሚ ባለድል የተቀበልንባት፣

❖ከአሮጌው፡ ወደዐዲሱ ዓመት የምንሸጋገርባትን ትንሿን ትርፍ የጳጕሜን ወር፡ በንስሓ፥ በጋድ ጾምነትና ንኡስ ሱባዔነት፡ የምስጋና ጾምና ጸሎት አድርገን ያሳለፍንባት መኾኗ ሊዘከር [ሊታሰብ] ይገባል።

፭ኛ፦ በቀን መቍጠሪያው፡ እያንዳንዱ ሠንጠረዥ ግርጌ፡ ለየወሩ የተመደቡ ምንባቦች ተሰናድተዋል። እነዚህ ምንባቦች የተዘጋጁት፡ በሳምንቱ የሥራ ቀኖች፡ በየዕለቱ፡ ለጧትና ለማታ፡ እጅግ ቢያንስ፡ ኹለት ምዕራፎችን፥ እንዲሁም፡ በየሰንበቱ፥ በሌሎቹም፡ የበዓላትና የዕረፍት ጊዜያት፡ በተቻለ መጠን፡ ምዕራፎቹን ጨማምሮ በማንበብ፡ ከቃለ-እግዚአብሔር ዝክረ-ነገር ላለመራቅ እንደሚቻል በመገመት ነው። መዝሙረ ዳዊት፡ በየቀኑ፡ በጸሎት መልክ ስለሚደገም፡ በምንባቡ ውስጥ አልታከለም፤ አልተካተተም።

፮ኛ፦ ጾሙና ጸሎቱ፥ የሱባዔው ጭምር፥ ምንባቡም፡ በግል፥ በቤተሰብ፥ ወይም፡ በኅብረት በመሰባሰብ ሊካኼድ ይቻላል።

፯ኛ፦ ይህን የቀን መቍጠሪያ፣ እንዲሁም፡ "**አዳምና ሔዋን፡ በኢትዮጵያ!**" በሚል፡ዓቢይ ርእስ ሥር፡ "**አንደኛ መጽሐፍ፡ ኢትዮጵያዊው፡ በጦብያ ፍለጋ!**"፥"**ኹለተኛ መጽሐፍ፡ ኢትዮጵያዊው፡ በእውነት ፍለጋ!**" እና "**ሦስተኛ መጽሐፍ፡ ኢትዮጵያዊው፡ በዕውቀት ፍለጋ!**" በተጨማሪም፡ በኢትዮጵያኛ እና በእንግሊዝኛ የተዘጋጁ፡ **«የቅዱሱ ኪዳን ሥርዓተ ትምህርት፡ ለኢትዮጵያ ሕፃናት፤ "አንደኛ እና ኹለተኛ መጻሕፍት"»** የሚል አርእስት ያላቸውን ዕትሞች እና እየታተሙ ያሉትን፥ ከእነዚህ በተጨማሪ፡"**ምሥራች! ከእናት ኢትዮጵያ፤ ለኢትዮጵያ ልጆች፤ ስለኢትዮጵያዊነት**"፥ደግሞም፡"**ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት**" በሚል አጠቃላይ አርእስት ሥር፡ "**አንደኛ መጽሐፍ**"፥ "**ኹለተኛ መጽሐፍ**" እና "**ሦስተኛ መጽሐፍ**" ተብለው፡ በተከታታይ የወጡትን፥ እንዲሁም፡ ቀደም ብለው፡ "**ምናሴ፡ የመከራዬ ደስታ፡ ዓለምን ረታ!**"፥ "**ኢትዮጵያዊው፡ በማንነቱ ፍለጋ!**"፥ "**ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ!**" እና **Ethiopia: The Classic Case** በሚሉ አርእስት፣ እነዚህ ኹሉ፡ ለመጀመሪያ ጊዜ፥ አንዳንዶቹም፡ ለኹለተኛና ሦስተኛ ጊዜያት ታትመው የወጡትንና እየተሠራጩ ያሉትን፥ ሌሎችንም፡ ወደፊት እየታተሙ የሚወጡትን ዕትሞችና መጻሕፍት ለማግኘት፡ የጎዋ ሰሌዳችንን መጎብኘት፥ እንዲሁም፡ ከዚህ በታች በተመለከቱት፡ ባሳታሚው አድራሻዎችና የመገናኛ መስመሮች፡ መጠየቅና መጠቀም ይቻላል።


<u>አሳታሚ እና አከፋፋይ</u> | <u>Publisher & Distributor</u>

**ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት።** | **Ethiopia: The Kingdom of God.**

መልእክት ሣጥን ቍጥር ፰፻፲፪ | Post Office Box 812

**<u>ስልክ ቍጥር</u>**፦ 0፲፩-፬-፲፮-፲፰-፹፭ | <u>Tel.</u>፦ (011-4-16-18-85)

**<u>የኪስ ስልክ ቍጥር</u>**፦ 0፱፳-፹፬፹፰፲፯፤ 0፱፳፱-፲፯፵፬፶፭፤ 0፱፲፩-፷፰፵፬፶፪።

**<u>Cellphon</u>**e፦ (0920-84 88 17 ; 0929-17 44 55 ; 0911-68 44 52)

**ዐዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ።** Addis Abeba, ETHIOPIA

**ወይም** or

**P. O. Box 43262 ~ Washington, DC 20010-9262 ~ USA.**

**Tel.: 301-587-8074 ~ Fax.: 301-587-1971** <u>Cellphone:</u> 202-594-1240

Email:info@ethkogserv.org Web Site:www.ethiopiathekingdomofgod.org


**በ፳፻፱ [በ፪ሺ፱] ዓመተ-ምሕረት፡ ንቡረ እድ ኤርምያስ፡ በሕይወተ ሥጋ ዘመኑ ማብቂያ፡ የኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ፳፻፲ [፪ሺ፲] ዓመተ-ምሕረት ቀን መቍጠሪያን እና የዐዲስ ዓመት መልእክትን፡ እንደባለፉት አያሌ ዓመታት፡ በዘመን አቆጣጠር ሥርዓቷ መሠረት፡ አዘጋጅቶ ማቅረቡ ይታወቃል። ይህ፡ የዘንድሮው፡ የ፳፻፲፱ [፪ሺ፲፱] ዓመተ ምሕረት የዐዲስ ዓመት መልእክትና የቀን መቍጠሪያ ዝግጅትም፡ በእግዚአብሔር ቸርነት፡ በዚህ መልክ ሊቀርብ በቅቷል።**

† † †

# ፪ሺ፲፱ (፳፻፲፱) ዓመተ ምሕረት ወርኀ መስከረም ዘመነ ሉቃስ ብሥራታዊ [ወንጌላዊ]

2019 Era of Mercy, Month of Meskerem (Sept.-Oct., 2026), Year of Luke the Evangelist

| እሑድ<br>ሰንበት ዝልፍት<br>Sunday | ሰኞ<br>Monday | ማግሰኞ<br>Tuesday | ረቡዕ<br>Wednesday | ሓሙስ<br>Thursday | ዓርብ<br>Friday | ሰንበት<br>Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| **ማስታወሻ**:-<br>*ከቅዱሱ ኪዳን፡ ለሰው ዘር፡ የመጨረሻ፡ የማንቂያ እና የማስጠንቀቂያ ደወል፡ በኒው-ዮርኩ የ፲፱፻፺፬ ዓ.ም. የቃጠሎ ግድያና ዕልቂት የተሰማባት፡ መስከረም ፩ (9/11):: | | | | | ፩ የድንግል ማርያም 11*<br>እና የኢየሱስ መሲሕ ልደታት።የኢትዮጵያ ነጻነት።<br>ኪዳነ አዳም ወሔዋን።<br>ቅዱስ ራጉኤል፡ሊቀ መላእክት። ቅዱስ ዮሓንስ መጥምቅ። በርተሎሜዎስ፡ ከ፲፪ቱ ሐዋርያት ፩ዱ። | ፪ 12<br>**ዮሓንስ መጥምቅ።** |
| ፫ 13<br>**ገዳማዊ አንበሰ ኢትዮጵያዊ** | ፬ 14 | ፭ ሄሮድስ 15<br>የፈጃቸው ሕፃናት።<br>የአሕመድ ግራኝን ወረራ፡ በሃይማኖት ተቋቁሞ የተጋደለ፡ አጼ ንብለ-ድንግል። | ፮ 16<br>**ኢሳይያስ ነቢይ።** | ፯ 17<br>**ኤልሣቤጥ**<br>ኢትዮጵያዊቷ የመጥምቁ ዮሓንስ እናት።<br>መናኔ መንግሥት **አጼ ተክለ-ሃይማኖት።** | ፰ 18<br>**ግዝረተ-ኢየሱስ።** | ፱ 19 |
| ፲ **አጼ** 20<br>**መስቀል።**<br>ግማደ መስቀሉ በ፲፩ኛው ፻ ዓመት በ፩ኛ አጼ ዳዊት ወደ ኢትዮጵያ ገባ። | ፲፩ 21<br>**አጼ በካፋ፡**<br>ስመ-ጥሩው ምሁር መሪ። | ፲፪ 22<br>ስለንስጥሮስ ኑፋቄ፡ የ፪፻ ሊቃውንት ጉባኤ፡ በኤፌሶን። | ፲፫ 23 | ፲፬ 24 | ፲፭ 25 | ፲፮ ኪዳነ 26<br>**ኖኅ።**<br>**ደመራ፡**<br>ለመስቀል የችቦ እሳት፡ የዛፍ አጠና ዎችን መደማመር። |
| ፲፯ 27<br>**በዓለ መስቀል።**<br>**ኢየሱስ መሲሕ የተሠዋበት እውነተኛው መስቀል ተገኘ።** | ፲፰ 28<br>ኢትዮጵያዊው ገዳማዊ **ኤዎስጣቴዎስ** ስለቅዳሜ ሰንበትነት ረታ። | ፲፱ 29 | ፳ 30<br>የኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልጋይ ኪዳናዊው ቄስ፡ ንቡረ-እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ ዘአኰስም ጽዮን ዕረፍት። | ፳፩ 1<br>**የቅድስት ድንግል ማርያም ፍልሰተ ዕርገት።**<br>ዜና መስቀል፡ በግሼን ማርያም የሚነገርበት። | ፳፪ 2 | ፳፫ 3 |
| ፳፬ 4<br>**ኪዳነ መልከ ጼዴቅ** | ፳፭ 5<br>**ዮናስ ነቢይ።**<br>የክረምት (የዝናም)ወራት ማብቂያ። | ፳፮ 6<br>የመፀው (የጽጌ=የአበባ) ወራት | ፳፯ 7 | ፳፰ 8<br>**ኪዳነ አብርሃም** | ፳፱ 9 | ፴ 10 |

"ወፈለግ ይወጽእ እምቅድሜሁ፡ ከመ ይሥቅያ ለገነት፤ ወእምህየ ይትፈለጥ፡ ለአርባዕቱ መአዝነ ዓለም። ...ወስሙ ለካልእ ፈለግ፡ 'ግዮን'፤ወውእቱ ዘየዐውድ ኵሎ ምድረ-ኢትዮጵያ። ...ወነሥአ እግዚአብሔር፡ ለዕጓለ-እመሕያው ዘገብሮ፤ ወሤሞ ውስተ ገነት፡ ከመ ይትገበራ፤ ወይዕቀባ። ገነትንም ያጠጣ ዘንድ፡ ከፊትለፊቱ፡ ወንዝ ይወጣ ነበር፤ ከዚያም፡ ወደአራቱ የዓለም ማእዘኖች ይከፈላል። ...የኹለተኛውም ወንዝ ስሙ፡ 'ግዮን' ነው፤ እሱም፡ የኢትዮጵያን ምድር፡ ዙሮ የሚያጠጣ ነው። ...እግዚአብሔርም፡ የፈጠረውን ሰው ወስዶ፡ ያርሳት፥ ይቆፍራት፥ ይጠብቃትና ይንከባከባት ዘንድ፡ በገነት ላይ ሾሞ፡ በዚያ አኖረው።" [ዘልደት (ዘፍጥ.) ፪፥ ፰-፲፯።]

| | |
|---|---|
| የመስከረም ወር ምንባብ:- | ኦሪት ዘልደት [ዘፍጥ.] እና መጽሓፈ ጥበብ። |

# ፪ሺ፲፱ (፳፻፲፱) ዓመተ ምሕረት ወርኀ ጥቅምት ዘመነ ሉቃስ ብሥራታዊ [ወንጌላዊ]

2019 Era of Mercy, Month of T'q'mt (Oct.-Nov., 2026), Year of Luke the Evangelist

| እሑድ<br>ሰንበት ዝልፍት<br>Sunday | ሰኞ<br>Monday | ማግሰኞ<br>Tuesday | ረቡዕ<br>Wednesday | ሓሙስ<br>Thursday | ዓርብ<br>Friday | ሰንበት<br>Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ፩ 11<br>**የጽጌ ማሕሌት** መግቢያ። | ፪ 12<br>ገዳማዊ ሕርያቆስ፡ የቅዳሴ ማርያም ደራሲ። | ፫ 13 | ፬ **አጼ** 14<br>**አብርሃ ወአጽብሓ** የቅዱሱ ኪዳን ክርስትናን በኢትዮጵያ ያስፋፉ | ፭ 15 | ፮ **ነቢይት** 16<br>ሓና፡ የነቢዩ ሳሙኤል እናት።<br>ከ፱ኙ ቅዱሳን ፩ዱ ገዳማዊ **ጰንጠሌዎን** | ፯ 17 |
| ፰ 18<br>**የጽጌ ማሕሌት።** | ፱ **አጼ ዳዊት** 19<br>የኢየሱስ መሲሕን ግማደ መስቀል፡ ከኢየሩሳሌም ያስመጣና "ዓባይን እገድባለሁ!" እያለ በዚያ የሚኖሩ ክርስቲያኖችን፡ ከእስላሞች ጥቃት ያዳነ። | ፲ **ኢየሱስ** 20<br>**መሲሕ** በ፭ ቀኑ፡ በእናቱ ዕቅፍ ቤተ-መቅደስ የገባበት።<br>በዓለ-ስምዖን።<br>ሓና ነቢይት።<br>አጼ ፋሲል፡ ካቶሊክነትን ተቃውሞ ተዋሕዶነትን አጸና፡፡ | ፲፩ 21<br>**የሕፃኑ ኢየሱስና የቅድስት እናቱ ድንግል ማርያም ስደት መታሰቢያ ጾም መግቢያ፡፡** | ፲፪ 22<br>**ማቴዎስ፡** ብሥራታዊው [ወንጌላዊው] ከ፲፪ቱ ሓዋርያት፩ዱ።<br>ቅዱስ ድሜጥሮስ፡ የቀንና የዘመን አቈጣጠርን ያስተካከለ። | ፲፫ 23 | ፲፬ **ፊልጶስ**24<br>ሓዋርያ፡ ኢትዮጵያዊዉን ጃንደረባ፡ አቤሜሌክን ያጠመቀ።<br>ገዳማዊ **ዘሚካኤል** አረጋዊ፡ከ፱ኙ ቅዱሳን ፩ዱ።<br>**ገብረ-ክርስቶስ።** |
| ፲፭* 25<br>የንቡረ-እድ (ቄስ) ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ ዘአኵስም ጽዮን የሸኝት በዓል (ግብዓተ መሬት) በቅዱስ ራጉኤል ወኤልያስ ርዕሰ አድባራት ተከናወነ።<br>**የጽጌ ማሕሌት።** | ፲፮ 26 | ፲፯ ቀዳሚው 27<br>ሰማዕት **እስጢፋኖስ** የሹመቱ መታሰቢያ።<br>**ዲዮስቆሮስ** ኢትዮጵያዊ፡ የግብፅ ሊቀ-ካህናትና የተዋሕዶ ሃይማኖት ተጋዳይ፥ የአኰቴተ-ቍርባን ቅዳሴውደራሲ | ፲፰ 28 | ፲፱ **አጼ** 29<br>**ይምራሕ** ቀዳሚዎቹን የእስልምና ስደተኞች በኢትዮጵያ አስተናግዶ የሸኘውና እነርሱ፡"ነጋሺ" የሚሉት፡ኢትዮጵያዊ ንጉሥ። | ፳ 30 | ፳፩ 31 |
| ፳፪ **ሉቃስ** 1<br>ብሥራታዊው[ወንጌላዊው]<br>**የጽጌ ማሕሌት።** | ፳፫ 2 | ፳፬ 3 | ፳፭ 4 | ፳፮ 5 | ፳፯ 6 | ፳፰ 7<br>**አማኑኤል።** ገዳማዊ ይማአታ ከ፱ኙ ቅዱሳን ፩ዱ |
| ፳፱ 8<br>**የጽጌ ማሕሌት ፍጻሜ።** | ፴ 9 | ማስታወሻ፡-*በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ የመጨረሻው የአኵስም ጽዮን ንቡረ እድ፡ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ ዓባይነሽ፡ሰንበት [ቅዳሜ]መስከረም ፳ ቀን፣ ፳፻፲ ዓ.ም. ዐረፈ። በዓለ ሸኙቱም [ግብዓተ መሬቱ]፡ ረቡዕ ጥቅምት ፲፭ ቀን፣ ፳፻፲ ዓ.ም. በቅዱስ ራጉኤል ወኤልያስ ርዕሰ አድባራት ተፈጸመ። ይህ ዕለት፥ መንፈስ ቅዱስ ባወቀ፡ከዛሬ ፺፬ ዓመታት በፊት፥ በጥቅምት ፲፭ ቀን ፲፱፻፳፭ ዓ.ም.፥ ንቡረ እድ (ቄስ) ኤርምያስ ከበደ፡ በቤተክህነት ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅነት የአገልግሎት ዘመኑ: ከረቂቁ አንስቶ ያዘጋጀው የሰበካ ጉባዔ መተዳደሪያ ህግና ደንብ የዐዋጅ ቃል፡ በነጋሪት ጦማር የታወጀበት ቀን ነው። (ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ ገጽ ፩፻፴፫-፩፻፴፬) | | | | |

"ወይቤሎ እግዚአብሔር አምላኩ ለኖኅ፡- 'ጊዜሁ ለዕጓለ-እመሕያው፡ በጽሓ ቅድሜየ፡እስመ መልአ ዐመፃ ዲበ ምድር እምኔሆሙ፤ወናሁ አነ እደመስሶሙ እምድር። ...ባእ አንተ፥ ወኵሉ ቤትከ፡ውስተ ታቦት፤እስመ ኪያከ ረከብኩ ጻድቀ በቅድሜየ፡በዛቲ ትውልድ።...ወገብረ ኖኅ፡ኵሎ ዘአዘዘ እግዚአብሔር አምላኩ።...ወዐጸዋ እግዚአብሔር ለታቦት፡እምአፍኣሃ፤ወኮነ ማየ አይኅ ላዕለ ምድር፡፵ መዓልተ፥ወ፵ ሌሊተ፤ወመልአ ማይ፤ወአልዓላ ለታቦት፤ወተለዓለት እምድር።" "እግዚአብሔር አምላኩ፡ኖኅን፡ እንዲህ አለው፡- 'በሰው ላይ፡ፍርድ የሚሰጥበት ጊዜ፡በፊቴ ደረሰ!ከእነርሱ የተነሣ፡በምድር ላይ የግፉ ጽዋ ሞልቷልና፤እነሆ፡እኔም፡ከምድር አጠፋቸዋለሁ።...አንተን ግን፡በዚህ ትውልድ መካከል፡በፊቴ፡እውነተኛ ሰው ኾነህ አግኝቼሃለሁና፡አንተ፡ከቤተሰብህ ኹሉ ጋራ፡ወደመርከብ ግባ!' ኖኅም፡ፈጣሪው እግዚአብሔር እንዳዘዘው አደረገ።...እግዚአብሔርም፡መርከቧን፡በውጭ በኩል ዘጋት፤በምድር ላይ፡፵ ቀንና ፵ ሌሊት፡ የጥፋት ውኃ ዘነበ፤ውኃውም መልቶ፡መርከቢቱን አንሳፈፋት፤ምድርንም ለቀቀች።" **የጥምቀት ምሳሌ ለኾነው፡ለመጀመሪያው ሃይማኖታዊ ጉዞ፡ የኢትዮጵያ [ቀይ] ባሕርን አቋርጣ፡አራራት ተራራ ላይ ለማረፍ፡ከኢትዮጵያ ተነሣች።** (ዘልደት [ዘፍጥ.] ፯፥ ፩-፲፫፤ ፯፥ ፩-፳፬።)

| የጥቅምት ወር ምንባብ፡- | መጽሓፈ ሩት እና መጽሓፈ ሲራክ። |
|---|---|

## ፪ሺ፲፱ (፳፻፲፱) ዓመተ ምሕረት ወርኀ ኅዳር ዘመነ ሉቃስ ብሥራታዊ [ወንጌላዊ]

2019 Era of Mercy, Month of H'dar (Nov.-Dec., 2026), Year of Luke the Evangelist

| እሑድ<br>ሰንበት ዝልፍት<br>Sunday | ሰኞ<br>Monday | ማግሰኞ<br>Tuesday | ረቡዕ<br>Wednesday | ሓሙስ<br>Thursday | ዓርብ<br>Friday | ሰንበት<br>Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| **ማስታወሻ**:- | | ፩ **አጼ** 10<br>**ነአኵቶ ለአብ፡**<br>መንግሥቱን፡<br>በኢትዮጵያዊው<br>የመልከ-ጼዴቅ<br>ሥርዓት የመራ። | ፪ 11 | ፫ 12 | ፬ 13 | ፭ **ለንጊኖስ** 14<br>የተሰቀለ ጌታን፡<br>ጎኑን በጦር የወጋና<br>ኋላ አምኖ በሰማዕትነት<br>የተጋደለ።<br>**የስደት ጾም**<br>ማብቂያ። |
| ፮ **ቍስቋም** 15<br>**ሕፃኑ ኢየሱስ እና**<br>**ቅድስት እናቱ፡**<br>በስደት የቆዩባት<br>የኢትዮጵያ ገዳም<br>በዓል። | ፯ 16 | ፰ **አርባዕቱ** 17<br>እንስሳ፡ መንበረ<br>ሥላሴን የሚሸከሙ<br>፰ቱ ሕያዋን ፍጡራን፡<br>ሰው፥ ላሕም፥<br>አንበሳና ንሥር። | ፱ 18<br>ስለአርዮስ<br>ኑፋቄ፡የ፫፻፲፰<br>ሊቃውንት<br>ጉባኤ፡ በኒቅያ | ፲ 19 | ፲፩ 20<br>**ሓና ቅድስት**<br>ኢትዮጵያዊት<br>የድንግል<br>ማርያም<br>እናት። | ፲፪ 21<br>**ቅዱስ ሚካኤል**<br>**ሊቀ-መላእክት።**<br>**አጼ በእደማርያም**<br>ሃይማኖታዊው<br>ተጋዳይ |
| ፲፫ 22<br>**አእላፍ**<br>**መላእክት።** | ፲፬ **በደርግ** 23<br>የዓመፅና የክህደት<br>አገዛዝ፡ በ፲፱፻፷፯<br>ዓ.ም. በኢትዮጵያ<br>ባለሥልጣኖች ላይ፡<br>የግፍ ግድያ ተፈጸመ | ፲፭ 24 | ፲፮ 25<br>**የጾመ-ነቢያት**<br>**መግቢያ።** | ፲፯ 26<br>**ዐዲስ አበባ**<br>ከተማ፡<br>በ፲፰፻፹፱<br>ዓ.ም.<br>የተቈረቈረችበት | ፲፰ 27<br>**ፊልጶስ፡**<br>ከ፲፪ቱ<br>ሐዋርያት<br>፩ዱ። | ፲፱ 28 |
| ፳ 29 | ፳፩ **ኪዳነ ሙሴ** 30<br>**ሕፃን ማርያም፡በ፹**<br>**ቀኗ፡ በቤተመቅደስ**<br>**የቀረበችበት።**<br>**ማርያም ጽዮን።**<br>**ማክዳ ንግሥትና**<br>**ልጇ ምኒልክ።** | ፳፪ 1 | ፳፫ 2<br>**ቆርኔሌዎስ**<br>**ጻድቅ**<br>(የሓዋ.ምዕ. ፲) | ፳፬ 3<br>**፳፬ቱ**<br>**ካህናተ-**<br>**ሰማይ** | ፳፭ 4<br>**መርቆሬዎስ**<br>ሰማዕት። | ፳፮ 5<br>በናግራን (የመን)፡<br>ኢትዮጵያውያን/ያት<br>ሰማዕታት። በዚያ፡<br>**የአጼ ካሌብ ድል።**<br>**ኢየሱስ-ሞዐ**<br>ዘሓይቅ። |
| ፳፯ 6<br>**ገዳማዊ ሊቃኖስ**<br>**ኢትዮጵያዊ፡**<br>**ዘደብረ-**<br>**ቍንጽል።** | ፳፰ 7<br>**ገዳማዊ**<br>**ሊቃኖስ፡** ከ፱ኙ<br>ቅዱሳን ፩ዱ። | ፳፱ **የሊቀ** 8<br>**ሓዋርያት ጴጥሮስ**<br>**ደቀ-መዝሙር፡**<br>**ቀሌምንጦስ።**<br>የሰማዕታት መጨረሻ<br>**ጴጥሮስ።** | ፴ **አጼ** 9<br>**ገብረ መስቀል፡**<br>በዘመኑ **የቅዱስ**<br>**ያሬድ** ሙያና<br>የ፱ኙ ቅዱሳን<br>ዜና የገነነበት።<br>**የጾመ-ነቢያት**<br>ማብቂያ። | **ማስታወሻ**:- | | |

**"ወመልከ-ጼዴቅ አምጽአ ኅብስተ፥ ወወይነ፤ወካህኑ ለእግዚአብሔር ልዑል፤ወንጉሠ ሳሌም ውእቱ። ወባረኮ ለአብራም፤ወይቤሎ:- 'ቡሩኩ አብራም ለእግዚአብሔር ልዑል፣ዘፈጠረ ሰማየ ወምድረ! ወቡሩክ እግዚአብሔር ልዑል፡ዘአግብአ ለጸላእትከ፡ ውስተ እዴከ! ወወሀቦ አብራም፡ ዐሥራተ ዕድ፡እምኵሉ።** 'መልከ-ጼዴቅም፡የኅብስትና የወይኑን ቍርባን አመጣ፤እርሱም፡የገናናው እግዚአብሔር አገልጋይ፥የሳሌምም ንጉሥ ነው። አብራምንም:- 'አንተ፡ሰማይንና ምድርን ለፈጠረው፡ለገናናው እግዚአብሔር የተባረክህ ነህ! ጠላቶችህን፡በእጅህ የጣለልህ ገናናው እግዚአብሔር የተመሰገነ ነው!' ብሎ ባረከው።አብራምም፡ከገንዘቡ ዅሉ፡አሥራትን ሰጠው።"**የእስራኤል ልጆች አባት የኾነውን፡ አብርሃምን፡ ለመለኮታዊው የግርዛት ቃል ኪዳን ያበቃው፡ የኢትዮጵያ ልጆች አጼ የኾነው፡ የዚህ፡ የኢትዮጵያዊው መልከ-ጼዴቅ የክህነት አገልግሎትና ቡራኬ መኾኑን ማስተዋል ነው።** (ዘልደት [ዘፍጥ.] ፲፬፥ ፲፯-፳)

| | |
|---|---|
| የኅዳር ወር ምንባብ:- | ኦሪት ዘፀአት እና ትንቢተ ኤርምያስ። |

# ፪ሺ፲፱ (፳፻፲፱) ዓመተ ምሕረት ወርኀ ታኅሣሥ ዘመነ ሉቃስ ብሥራታዊ [ወንጌላዊ]

2019 Era of Mercy, Month of Tah'sas (Dec.,2026-Jan., 2027), Year of Luke the Evangelist

| እሑድ<br>ሰንበት ዝልፍት<br>Sunday | ሰኞ<br>Monday | ማግሰኞ<br>Tuesday | ረቡዕ<br>Wednesday | ሓሙስ<br>Thursday | ዓርብ<br>Friday | ሰንበት<br>Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ማስታወሻ፡-<br>*ከተራ፡ ለጥምቀት በዓል ዋዜማ፡ውኃ፡ ከወንዝ ተወስዶ የሚከተርበት (የሚጠራቀምበት)። | | | | ፩ 10<br>በዓለ ትስብእት፡ ኢየሱስ መሲሕ የተፀነሰበት።<br>ብሥራተ ገብርኤል።<br>ኤልያስ ነቢይ።<br>ቤትሳባ ኢትዮጵያዊት፡ የሰሎሞን እናት። | ፪ 11 | ፫ ሕፃን 12<br>ማርያም፡ በስእለት ለቤተ-መቅደስ የተሰጠችበት።<br>ቅዱስ ፋኑኤል ሊቀ-መላእክት።<br>ዳግማዊ አጼ ምኒልክ።<br>ሀብተ-ጊዮርጊስ፡ አባመላ። |
| ፬ 13<br>እንድርያስ፡ ከ፲፪ቱ ሓዋርያት ፩ዱ። | ፭ የቅዱሱ 14<br>ኪዳን ማስጠንቀቂያ ኾኖ፡በ፲፱፻፶፫ ዓ.ም.፡ በክብር ዘበኛ ጦር አዛዥ የተመራው፤ ብዙ ደም ያፈሰሰው ያልጋ ግልበጣ ሙከራ። | ፮ የዐዲስ 15<br>ዓለም ማርያም ሰማዕታት ካህናት፤ በ፲፱፻፴፫ ዓ.ም. በፋሺስት ጣልያን የተሠየፉት። | ፯ 16<br>ፅንሰታ ለማርያም (ድንግል ማርያም የተፀነሰችበት) | ፰ 17<br>ኢትዮጵያዊው ገዳማዊ ኪሮስ። | ፱ 18<br>ገዳማዊ በአሚን ኢትዮጵያዊ | ፲ 19<br>በወሎ፡ደብረ እግዚአብሔርና የሓይቅ መካነ-እስጢፋኖስ፡ በአሕመድ ግራኝ ጦር ተበዘበዙ። |
| ፲፩ 20<br>ስብከት። | ፲፪ 21<br>ኢትዮጵያዊው ገዳማዊ ሳሙኤል፡ የዋልድባው። | ፲፫ 22 | ፲፬ 23<br>በ፲፱፻፳፰ ዓ.ም. የፋሺስት ጣልያን አየር ኃይል፡ በኢትዮጵያ ላይ፡ የመርዝ ጢስ ማዝነብ ጀመረ። | ፲፭ 24 | ፲፮ 25 | ፲፯ 26 |
| ፲፰ ብርሃን። 27<br>በአኲስሙ ሊቀ-ካህናት እንበረም ተልኮ፡ ያልታሰበውን የግብፅን የጵጵስናን አገዛዝ ወደኢትዮጵያ ያመጣ ፍሬምናጦስ። | ፲፱ 28<br>ቅዱስ ገብርኤል ሊቀ መላእክት ፫ቱ ደቂቅን፡ ከባቢሎን እሳት አዳነ። | ፳ 29 | ፳፩ 30 | ፳፪ 31 | ፳፫ 1<br>ኪዳነ ዳዊት | ፳፬ 2<br>የእቲሳው፡ እጨጌ ተክለ-ሃይማኖት ልደት። |
| ፳፭ ኖላዌ። 3<br>የመፀው (የጽጌ) ወራት ማብቂያ። | ፳፮ 4<br>የሓጋይ (የበጋ) ወራት መግቢያ። | ፳፯ 5<br>አጼ ኢያሱ ብርሃን ሰገድ። | ፳፰ 6 | ፳፱ 7<br>የቅዱስ አጼ ላልይበላል ልደት። | ፴ 8<br>ከተራ* [የጋድ ጾም] | ማስታወሻ፡- |

ኢትዮጵያዊው መልከ-ጼዴቅ ከባረከው በኋላ፡ እግዚአብሔር ተገልጦለት፡ **"አነ ውእቱ እግዚአብሔር ፈጣሪከ፡ ዘሖርኩ ቅድሜከ! አሥምር ቅድሜየ! ወኩን ንጹሓ! ወእሠይም ኪዳነ፡ ማእከሌየ ወማእከሌከ! ወአብዝኀከ ጥቀ!... ወኢይሰመይ እንከ ስምከ 'አብራም'፤ አላ፡ 'አብርሃም' ይሰመይ! እስመ አበ ብዙኃን አሕዛብ ረሰይኩከ።** በፊትህ የኼድሁ ፈጣሪህ እግዚአብሔር፡ እኔ ነኝ! በፊቴ፡በጎ ነገር አድርግ! ንጹሕ ኹን! በእኔ እና በአንተ መካከል ኪዳንን እሠይማለሁ!እጅግም አበዛሃለሁ!... እንግዴህም፡ስምህ፡ 'አብራም' አይባልም፤ 'አብርሃም' እንጂ። ለብዙዎች አሕዛብ፡ ወላጅ አድርጌሃለሁና።" ያለው፡ ይህ የሃይማኖትና የምግባር ሰው፡ከተገረዘና ሣራ ከሞተች በኋላ፡ ኢትዮጵያዊቷን ኬጡራን፡ በሚስትነት አግብቶ፡ **"ምድያማውያን"** የተባሉ፡ የኢትዮጵያን ልጆች በመውለዱ፡ ለኢትዮጵያዊነት፡ አንዱ አብነት ኾኗል። (ዘልደት [ዘፍጥ.] ፲፯፥ ፩-፭፤ ፳፤፳፭።)

| የታኅሣሥ ወር ምንባብ፡- | መጽሓፈ ሳሙኤል እና ትንቢተ ሕዝቅኤል። |
|---|---|

# ፪ሺ፲፱ (፳፻፲፱) ዓመተ ምሕረት ወርኀ ጥር ዘመነ ሉቃስ ብሥራታዊ [ወንጌላዊ]

2019 Era of Mercy, Month of TT’rr (Jan.-Feb., 2027), Year of Luke the Evangelist

| እሑድ ሰንበት ዝልፍት Sunday | ሰኞ Monday | ማግሰኞ Tuesday | ረቡዕ Wednesday | ሓሙስ Thursday | ዓርብ Friday | ሰንበት Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| **ማስታወሻ፡-** | | | | | | ፩ **ጥምቀት፤** 9 **በዓለ አስተርእዮ።** ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ **አቤሜሌክ** [ባኮስ]። በቅዳሴ ጸሎቱ፡ የጥምቀት ወንዝ የቆመለት የተጕለቱ ታቦት-ዋሻ ካህን፡ **ትልቁ ቀሲስ ወልደ-ኢየሱስ።** |
| ፪ 10 **አቤል ጻድቅ።** | ፫ 11 **ገዳማዊ መጣዕ** ዘሊባኖስ ኢትዮጵያዊ። | ፬ 12 **ዮሓንስ** ብሥራታዊ [ወንጌላዊ] ከ፲፪ቱ ሓዋርያት፩ዱ | ፭ 13 | ፮ 14 **ኖኅ።** **ዕርገተ ኤልያስ።** | ፯ 15 **የአስተርእዮ ቅድስት ሥላሴ** | ፰ 16 |
| ፱ 17 | ፲ 18 | ፲፩ 19 | ፲፪ 20 **ድንግል ማርያም፡ እግዝእተብሔር እም የተዋሓደቻት፥ ልጇም ኢየሱስ፡ እውነተኛው መሲሕ መኾናቸው፡ በቃና ዘገሊላ ሠርግ ተገለጠ።** | ፲፫ 21 **ሕንደቄ ንግሥተ-ኢትዮጵያ፡** በ፴፬ ዓ.ም. በጃንደረባዋ አማካይነት፡ ክርስትና ወዳገርዋመጣ | ፲፬ 22 እንበረም ሊቀ-ካህናት ዘአኵስም በ፫፻፳፭ ዓ.ም. የኢትዮጵያን ሥርዓተ-ቤተክርስቲያን አሟላ። | ፲፭ 23 **ቅዱስ ቂርቆስ፡ የ፫ ዓመት ሕፃን ሰማዕት።** |
| ፲፮ 24 **ቅድስት ኢየሉጣ ሰማዒት፤ የሕፃኑ ቅዱስ ቂርቆስ እናት።** | ፲፯ **ቅዱስ** 25 **እስጢፋኖስ** እንደመምህሩ፡ ኢየሱስ መሲሕ ለእውነት በይፋ መስክሮ የተሠዋ ቀናዒ ካህንና ቀዳሚ ሰማዕት። | ፲፰ 26 **ዝርወተ ዐፅሙ ለጊዮርጊስ** | ፲፱ 27 | ፳ 28 | ፳፩ 29 **የቅድስት ድንግል ማርያም ፍልሰት ወደገነት። (በዓለ-ፍልሰታ፡ ዘአስተርእዮ ድንግል ማርያም)** | ፳፪ 30 |
| ፳፫ **መርዓዊ** 31 ፴ የበዓለ 7 **ኢትዮጵያ ማብቂያ።** | ፳፬ 1 | ፳፭ 2 | ፳፮ 3 | ፳፯ 4 **ዕርገተ-ሄኖክ።** | ፳፰ 5 የበዓለ **ኢትዮጵያ መግቢያ።** | ፳፱ 6 **በዓለ ኢትዮጵያ።** |

ሙሴ፡ ከግብፅ፡ በስደት፡ ወደኢትዮጵያ መጥቶ፡ ስለኢትዮጵያዊነት፡ ከኢትዮጵያዊው ካህን፡ ከዮቶር ተምሮ፡ ካመነ በኋላ፡ የካህኑን ሴት ልጅ፡ ሲጳራን አገባ፤ የአማቱን በጎች ሲጠብቅ ሣለም፡ እነሆ፡ እግዚአብሔር ተገልጾለት፡ ያዘዘውን ኹሉ በመፈጸሙ፡ ኢትዮጵያዊነትን መቀበሉ፡ እውን ኾኗል። ከዚህ ኢትዮጵያዊነቱ የተነሣም፡ የኋላ ኋላ፡ በወንድሙና በእኅቱ ሳይቀር፡ ከእስራኤል ሕዝብ፡ በደል እንደደረሰበት ተጽፏል። ሙሴና የእስራኤል ሕዝብ፡ ገና፡ በምድረ-በዳ ሠፍረው ሣሉ፡ ጽላተ-ሕጉንና ታቦቱን ከእግዚአብሔር ከመቀበሉ በፊት፡ የሚቃጠልንና ሌላ መሥዋዕትን፡ ለእግዚአብሔር በማቅረብ፡ ሥርዓተ-ክህነትን፥ ስለሕዝብ አስተዳደርና ስለፍትሕ አሰጣጥም በማስተማር፡ የኢትዮጵያን እግዚአብሔራዊ ሥርዓተ-መንግሥት፡ አማቱ፡ ኢትዮጵያዊው ዮቶር፡ ለሙሴና ለአሮን፥ ለሕዝቡ ሽማግሌዎችም ኹሉ ማሳየቱ፡ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ተመዝግቧል። (ዘጸአ. ፫፥ ፩-፭፤ ፲፰፥ ፩-፳፯። ዘኍል. ፲፪፥፩-፲፭።)

| | |
|---|---|
| የጥር ወር ምንባብ፡- | መጽሓፈ ኢዮብ እና የማቴዎስ ብሥራት [ወንጌል]። |

# ፪ሺ፲፱ (፳፻፲፱) ዓመተ ምሕረት ወርኀ የካቲት ዘመነ ሉቃስ ብሥራታዊ [ወንጌላዊ]

2019 Era of Mercy, Month of Yekatit (Feb.-Mar., 2027), Year of Luke the Evangelist

| እሑድ<br>ሰንበት ዝልፍት<br>Sunday | ሰኞ<br>Monday | ማግሰኞ<br>Tuesday | ረቡዕ<br>Wednesday | ሓሙስ<br>Thursday | ዓርብ<br>Friday | ሰንበት<br>Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| **ማስታወሻ፡-**<br>ጥር ፴፡ የበዓለ ኢትዮጵያ ማብቂያ። | ፩ 8<br>ስለ መቅዶንዮስ ኑፋቄ የ፻፶ ሊቃውንት ጉባኤ በቍስጥንጥንያ። | ፪ 9 | ፫ **የግሼን** 10<br>**ማርያም**<br>አምባ፡ በ፲፭፻፴፪ ዓ.ም. በአሕመድ ግራኝ ጦር ተመዘበረ። | ፬ 11<br>**ጣይቱ ብጡል፣ ብርሃን ዘኢትዮጵያ** | ፭ 12 | ፮ **ማርያም** 13<br>**እንተ ዕፍረት** መሲሕን በእንባዋ፡ እግሩን ያጠበች። |
| ፯ 14<br>**ዘወረደ**<br>(ቅበላ)። | ፰ 15<br>**የዓቢይ ጾምና የጾመ ሕርቃል መግቢያ።** | ፱ 16 | ፲ 17<br>**ያዕቆብ ወልደ እልፍዮስ፡**<br>ከ፲፪ቱ ሓዋርያት ፩ዱ። | ፲፩ 18 | ፲፪ 19<br>በ፲፱፻፳፱ ዓ.ም. የፋሺስት ጣልያን ጦር በሰላማዊው የዐዲስ አበባ ሕዝብ ላይ የፈጸመው ግድያና ዕልቂት። | ፲፫ 20 |
| ፲፬ 21<br>**ቅድስት።** | ፲፭ 22<br>**የመሲሕ ኢየሱስ የአርባ ቀን ጾም መነሻ።** | ፲፮ 23<br>**ኪዳነ ምሕረት፡ በድንግል ማርያምና በኢየሱስ መሲሕ የተገኘ።**<br>በ፲፱፻፸፱ ዓ.ም. የጎግ ማጎግ የሱማሌ ወረራ፡ ካራማራ ድል ላይ፡ **የቅዱሱ ኪዳን ጥበቃ፡** በገሃድ ታየ። | ፲፯ 24 | ፲፰ 25<br>**አዝማች ደገልሓን** የአሕመድ ግራኝን ጦር በቆራጥነት የተዋጋ ጀግና ኢትዮጵያዊ | ፲፱ 26 | ፳ 27 |
| ፳፩ **ምኲራብ።** 28<br>ከጉዲት አገዛዝ በኋላ፡ በ፱፻፴፫ ዓ.ም. በአገዉ (በዛጔው) **መርሓ-ተክለ ሃይማኖት፡** የኢትዮጵያ መልከ ጼዴቃዊ ሥርዓተ-መንግሥት ተመለሰ። | ፳፪ 1 | ፳፫ 2<br>**የአድዋ ድል! ኢትዮጵያ፡ ኃይሏ፡ በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖቷ መኾኑ የተረጋገጠበት።** | ፳፬ 3 | ፳፭ 4 | ፳፮ 5 | ፳፯ 6<br>ግራኝ አሕመድ በ፲፭፻፴፭ ዓ.ም **ድል ኾነ።** |
| ፳፰ 7<br>**መጻጕዕ።** | ፳፱ 8 | ፴ 9 | **ማስታወሻ፡-** | | | |

**"ይሁዳ፡ ዕጓለ-አንበሳ! እምኀዘአትከ ዕርገ! ወልድየ! ሰከብከ፤ ወኖምከ፡ ከመ አንበሳ፥ ወከመ ዕጓለ-አንበሳ፡ አልቦ ዘያነቅሖከ። ኢይጠፍእ ምልክና፡ እምይሁዳ፤ ወምስፍና፡ እምአባሉ፤ እስከ አመ ይረክብ፡ ዘጽኑሕ ሎቱ። ወውእቱ፡ ተስፋሆሙ ለአሕዛብ። ...ወብዙኃን እለ በከዩ፤ ወአነሂ ምስሌሆሙ፤ እስመ አልቦ ዘተረክበ፡ ዘይደልዎ ይክሥታ፥ ወይርአያ፡ ለይእቲ መጽሓፍ፡ [እንተ ሀለወት] ውስተ የማኑ፡ ለውእቱ፡ዘይነብር ዲበ መንበር። ወይቤለኒ፡ አሓዱ፡ እምውስተ እልክቱ [፳፬ቱ] ሊቃናት፡- 'ኢትብኪ! ናሁ፡ ሞአ አንበሳ፡ ዘእምነገደ ይሁዳ፤ እምውስተ ሥርዉ ለዳዊት፤ ከመ ይፍትሓ፡ ለይእቲ መጽሓፍ፥ ወለማኅተሚሃ!'** የይሁዳ አንበሳ ደቦል! ከመደብህ ውጣ! ልጄ! እንደአንበሳ ተኛህ፤ አንቀላፋህም፤ እንደአንበሳ ደቦልም፡ ሊቀሰቅስህ የሚችል የለም። መንግሥት፡ ከይሁዳ፥ የሕዝብ አስተዳደርም፡ ከወገኑ አይወጣም፤ ይህ ሥልጣን፡ የሚጠበቅለትን፤ ለአሕዛብም ተስፋቸው የኾነውን፡ እርሱን እስከሚያገኝበት ጊዜ ድረስ። ...በዙፋኑም ላይ በተቀመጠው፡ በቀኝ እጁ ያለችውን መጽሓፍ ሊዘረጋ፥ ሊመለከታትም የሚገባው፡ ማንም ስላልተገኘ፡ ብዙዎች አለቀሱ፤ እኔም ዐብሬአቸው አለቀስሁ። ከእነዚያ [ከ፳፬ቱ] ሊቃናት መካከል፡ አንዱ፡- 'አታልቅስ! እነሆ፡ ከይሁዳ ነገድ የኾነውአንበሳ፤ እርሱም፡ የዳዊት ሥር፡ መጽሓፏን ይዘረጋ ዘንድ፥ ማኅተሚዋንም ይፈታ ዘንድ፡ ድል ነሥቷል!' አለኝ።" የሚለውን፡ የእግዚአብሔር ቃል፡ የኢትዮጵያ ልጆች፡ በሃይማኖት ተቀብለው፡ በምግባር ስለፈጸሙት፡ **እውነተኞቹ እስራኤል** እነርሱ መኾናቸው ተረጋግጧል። (ዘልደት [ዘፍጥ.] ፵፱፥ ፱-፲፤ ራእ. ፭፣ ፩-፭።)

| የየካቲት ወር ምንባብ፡- | ኦሪት ዘዳግም፥ ትንቢተ ዮናስ እና የማርቆስ ብሥራት [ወንጌል]። |
|---|---|

## ፪ሺ፲፱ (፳፻፲፱) ዓመተ ምሕረት ወርኀ መጋቢት ዘመነ ሉቃስ ብሥራታዊ [ወንጌላዊ]

2019 Era of Mercy, Month of Megabbit (Mar.-Apr., 2027), Year of Luke the Evangelist

| እሑድ ሰንበት ዝልፍት Sunday | ሰኞ Monday | ማግሰኞ Tuesday | ረቡዕ Wednesday | ሓሙስ Thursday | ዓርብ Friday | ሰንበት Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ማስታወሻ:- | | | ፩ አጼ 10<br>ዮሓንስ ፬ኛ:<br>የመተማው ሰማዕት<br>በድርቡሽ እስላም<br>ወራሪ የተሠየፈ። | ፪ 11 | ፫ 12 | ፬ 13 |
| ፭ 14<br>ደብረ ዘይት።<br>ገዳማዊ ገብረ<br>መንፈስ ቅዱስ። | ፮ 15 | ፯ 16 | ፰ 17<br>ማትያስ:<br>ከ፲፪ቱ<br>ሓዋርያት<br>፩ዱ። | ፱ 18 | ፲ 19 | ፲፩ 20<br>ገዳማዊ<br>አሌፍ:<br>ከ፱ኙ<br>ቅዱሳን ፩ዱ |
| ፲፪ 21<br>ገብር-ኄር። | ፲፫ 22 | ፲፬ 23 | ፲፭ 24 | ፲፮ 25 | ፲፯ 26 | ፲፰<br>27 |
| ፲፱ 28<br>ኒቆዲሞስ። | ፳ 29 | ፳፩ 30 | ፳፪ 31 | ፳፫ 1<br>ዳንኤል<br>ነቢይ። | ፳፬ 2<br>ንግሥት<br>ዘውዲቱ<br>ምኒልክ። | ፳፭ 3<br>የሓጋይ<br>(የበጋ)<br>ወራት<br>ማብቂያ |
| ፳፮ 4<br>ሆሣዕና።<br>የጸደይ<br>(የበልግ)<br>ወራት<br>መግቢያ | ፳፯ 5<br>**የሰሙነ ሕማማት መግቢያ።**<br>አጼ ገላውዴዎስ:<br>ኵትልክናን: በተዋሕዶነት<br>የተቋቋመ፤ በእስላም ወራሪ:<br>ሰማዕትነትን የተቀበለ። | ፳፰ 6<br>ቈስጠንጢኖስ<br>ቄሣር:<br>ስለሃይማኖትና<br>ስለፍትሓ-ነገሥት<br>ዝግጅት: የ፫፻፲፰<br>ሊቃውንት ጉባኤን:<br>በኒቅያ አሰባሰበ። | ፳፱ 7<br>የአይሁድ<br>ሸንጎ: ኢየሱስ<br>መሲሕን<br>ለመግደል<br>ወሰነ። | ፴ 8<br>**ጸሎተ ሓሙስ** | ማስታወሻ:- | |

"'ናሁ ይመጽእ መዋዕል!' ይቤ እግዚአብሔር፤ 'ወአቀውም ለዳዊት: ሠርፀ ጽድቅ፤ ወይነግሥ ንጉሥ: ዘይኄሊ፤ ወይገብር ጽድቀ፥ ወርትዐ: በዲበ ምድር። ...ወይሠርፅ ጽድቅ: በመዋዕሊሁ፤ ወብዙኅ ሰላም: እስከ የኀልፍ ወርኅ። ወይኴንን እምባሕር: እስከባሕር፤ ወእምአፍላግ: እስከአጽናፈ ዓለም። ይገንዩ ቅድሜሁ ኢትዮጵያ፤ ወጸላእቱሂ: ሐመደ ይቀምሑ። ...እግዚአብሔርሰ: ንጉሥ ውእቱ: እምቅድመ ዓለም፤ ወገብረ መድኃኒተ በማእከለ ምድር። ...አንተ ሰበርከ ርእሶ፥ ወቀጥቀጥከ አርእስቲሁ ለከይሲ። ወወሀብኮሙ ሲሳዮሙ: ለሕዝበ ኢትዮጵያ።' 'እነሆ: ለዳዊት: የእውነት ቍጥቋጥ የማስነሣበት ጊዜ ይመጣል! እርሱም: በምድር ላይ: እውነትንና ቅንነትን የሚያስብና የሚያደርግ ንጉሥ ይኾናል!' ይላል እግዚአብሔር። '...በዘመኑ: እውነት ትከሠታለች፤ የግብዝነቱም ወራት አልፎ: ሰላም ይበዛል። ከባሕር እስከባሕር፥ ከታላላቁ ወንዞች: እስከምድር ዳርቻ ያለውን ዓለም ያስተዳድራል። <u>የኢትዮጵያ ልጆች: ዜጎቹ ይኾናሉ</u>። ጠላቶቹም: አፈር ይበላሉ። ...እግዚአብሔርማ: ከዓለም አስቀድሞ: ንጉሥ ነው! በምድርም መካከል: መድኃኒትን አደረገ። ...አንተ: የእባቡን ራስ ሰበርህ! ራሶቹንም: ቀጠቀጥህ! <u>ለኢትዮጵያ ሕዝብህም: ሲሳያቸውን ሰጠሃቸው!</u>'"(ኤር. ፳፫፥ ፭። መዝ.፸፩፥ ፯-፱፤ ፸፫፥ ፲፪-፲፬)

| | |
|---|---|
| የመጋቢት ወር ምንባብ:- | ትንቢተ ኢሳይያስ እና የጳውሎስ መልእክታት። |

# ፪ሺ፲፱ (፳፻፲፱) ዓመተ ምሕረት ወርኀ ሚያዝያ ዘመነ ሉቃስ ብሥራታዊ [ወንጌላዊ]

2019 Era of Mercy, Month of Miazia (Apr.-May, 2027), Year of Luke the Evangelist

| እሑድ<br>ሰንበት ዝልፍት<br>Sunday | ሰኞ<br>Monday | ማግሰኞ<br>Tuesday | ረቡዕ<br>Wednesday | ሓሙስ<br>Thursday | ዓርብ<br>Friday | ሰንበት<br>Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| **ማስታወሻ:-** | | | | | ፩ 9<br>**የኢየሱስ መሲሕ መስቀለ-ሞቱ።** | ፪ 10<br>**ኢየሱስ መሲሕ በመቃብር ያረፈባት፡ ታላቋ ሰንበት።** |
| ፫ 11<br>**የኢየሱስ መሲሕ በዓለ ትንሣኤ።** | ፬ 12<br>**ማዕዶት** (በሕይወተ-ሥጋ እያሉ በመንፈስ ወደ ትንሣኤ ሕይወት መሻገር)። | ፭ 13<br>**ሕዝቅኤል** ነቢይ። | ፮ 14<br>**ዳግማዊ ቴዎድሮስ** አርበኛው አፄ መሪ። | ፯ **አዳም ሓሙስ** 15<br>የ፳ሺ፳፪ው ዓመት ተስፋ፡ ፍጻሜ።<br>ኢትዮጵያዊው ኢያቄም፡ የድንግል ማርያም ወንድ ወላጅ (አባት)። | ፰ 16<br>**ማርቆስ** ብሥራታዊ [ወንጌላዊ]። | ፱ 17 |
| ፲ 18<br>**ዳግም ትንሣኤ።** (ከፊተኛው የመንፈስ ትንሣኤ በኋላ ያለው የፍጻሜ ትንሣኤ መታሰቢያ)። | ፲፩ 19 | ፲፪ 20<br>ደብረ-ብርሃን፡ በ፲፫፻፳፫ዓ.ም በአሕመድ ግራኝ ተቃጠለ። | ፲፫ 21<br>በ፲፱፻፳፰ ዓ.ም. ፋሺስት ጣልያን፡ **ማኅበረ ሥላሴን፡** በአየር ኃይሉ ደበደበ። | ፲፬ 22 | ፲፭ ሦስት 23<br>የማኅበረ-ሥላሴ ገዳም አባሎች፡ በ፲፱፻፳፰ ዓ.ም. በፋሺስት የጣልያን ጦር ተገደሉ። | ፲፮ 24 |
| ፲፯ **ያዕቆብ** 25<br>**ወልደ ዘብዴዎስ፡** ከ፲፪ቱ ሓዋርያት፩ዱ | ፲፰ 26 | ፲፱ 27 | ፳ 28 | ፳፩ 29<br>**እጨጌ ዕንባቆም፡** ሰባኬ ሃይማኖት። | ፳፪ 30 | ፳፫ **ቅዱስ** 1<br>**ጊዮርጊስ** ሰማዕት። |
| ፳፬ 2 | ፳፭ 3 | ፳፮ 4 | ፳፯ **ኢትዮጵያ** 5<br>ነጻነቷና በፋሺስት ጣልያን ላይ የተቀዳጀችው ድል፡ **በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖቷ** መኾኑ ተረጋገጠ።<br>**ርክበ ካህናት።** | ፳፰ 6 | ፳፱ 7 | ፴ 8 |

"**ወንግሥተ ሳባ፡ ሰምዓት ስሞ ለሰሎሞን፤ ወስሞ ለእግዚአብሔር፤ መጽአት ትፍትኖ፡ ምስለ ጥበባ። ወቦአት ኢየሩሳሌም፡ በኃይል ክቡድ ፈድፋደ። ...ወቦአት ኀበ ሰሎሞን፤ ወተናገረቶ ኵሎ ዘሀሎ ውስተ ልባ። ...ወወሀበቶ ለሰሎሞን፡ ምእተ፥ ወዕሥራ መካልየ ዘወርቅ፥ ወአፈዋተ ፈድፋደ ብዙኀ፥ ወዕንቈ ክቡረ፤ ወአልቦ አመ መጽአ ብዙኀ አፈዋተ፡ ዘከመ አሜሃ፡ ዘወሀበት ንግሥተ ሳባ፡ ለሰሎሞን።** የሳባ ንግሥት፡ የሰሎሞንን ስም፥ የእግዚአብሔርም ስም፡ በእርሱ ሲጠራ በሰማች ጊዜ፡ ስለሃይማኖቱና ስለእውነተኛ ማንነቱ፡ በጥበቧ ትፈትነው ዘንድ፡ እጅግ ብዙ ከኾነ ሠራዊትና ጓዝ ጋር፡ ከኢትዮጵያ፡ ወደኢየሩሳሌም መጣች።...ወደሰሎሞንም ገባች፤ በልቧ ውስጥ ያለውን ኹሉ፡ ገልጣ ነገረችው። መቶ ሃያ የወርቅ መክሊትን፥ እጅግ ብዙ የኾነ ሽቱን፥ የከበረ ዕንቍንም [ሉልን] ሰጠችው። የዚያን ጊዜ፡ የሳባ ንግሥት፡ ለሰሎሞን የሰጠችውን፡ ያን የመሰለ ብዛት ያለው ስጦታ፡ ከዚያ ወዲያ አልመጣም።" የትንቢቱ ፍጻሜና ዘላለማዊው ንጉሥ ኢየሱስ መሲሕ፡ በምድር ላይ በተገለጠበት ጊዜ፡ ከእርሱ፡ ማስረጃ ምልክትን ለጠየቀው፡ ለዚያ፡ ከሃዲና ዓመፀኛ፥ ክፉና ዘማዊ ትውልድ፡ እንዲህ የሚል የመጨረሻ መልስን ሰጠ:- "**ንግሥተ አዜብ ትትነሣእ፡ አመ ዕለተ ደይን፡ ምስለ ዛ ትውልድ፤ ወትትፋትሓ፥ ወታስተኃፍራ፤ እስመ መጽአት እምአጽናፈ ምድር፡ ትስማዕ ጥበቢሁ ለሰሎሞን፤ ወናሁ፡ ዘየዐቢ እምሰሎሞን፡ ሀሎ ዝየ።** ንግሥተ አዜብ (ኢትዮጵያ)፡ በፍርድ ቀን፡ ከዚህ ትውልድ ጋር ተነሥታ፡ ትፋረደዋለች፤ ታሳፍረዋለችም። የሰሎሞንን ጥበብ ለመስማት፡ ከምድር ዳር መጥታለችና። እነሆም፡ ከሰሎሞን የሚበልጥ፡ ከዚህ አለ።" ከዚህ ፍርድ ለመዳን፡ "**ነገሥተ ምድር ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር! ወዘምሩ ለአምላክነ! ወለኢትዮጵያ፡ ዘታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር።** እናንተ፡ በምድር ያላችሁ የሰዎች መንግሥታት ኹሉ፡ ለፈጣሪያችሁ ለእግዚአብሔርና እጆቿን፡ ወደእርሱ አድርሳ (ዘርግታ) ለምትኖረው፡ ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ዘምሩ! ምስጋናችሁንም አቅርቡ!" (፩ ነገ. ፲፥ ፩-፲። ማቴ. ፲፪፥ ፵፪። መዝ. ፷፯፥ ፴፩-፴፪።)

| የሚያዝያ ወር ምንባብ:- | ትንቢተ ዳንኤል እና ራእየ ዮሓንስ። |
|---|---|

# ፪ሺ፲፱ (፳፻፲፱) ዓመተ ምሕረት ወርኀ ግንቦት ዘመነ ሉቃስ ብሥራታዊ [ወንጌላዊ]

2019 Era of Mercy, Month of G’nbot (May-June, 2027), Year of Luke the Evangelist

| እሑድ<br>ሰንበት ዝልፍት<br>Sunday | ሰኞ<br>Monday | ማግሰኞ<br>Tuesday | ረቡዕ<br>Wednesday | ሓሙስ<br>Thursday | ዓርብ<br>Friday | ሰንበት<br>Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ፩ ቅድስት 9<br>ድንግልማርያም<br>በሊባኖስ ተራራ<br>ላይ የመወለዷ<br>መታሰቢያ። | ፪ 10<br>ኢዮብ<br>ጻድቅ<br>ኢትዮጵያዊ። | ፫ 11 | ፬ 12 | ፭ 13<br>ኢትዮጵያውያኑ<br>ኤርምያስ ነቢይ፥<br>ደቀ-መዛሙርቱ፡<br>አቤሜሌክና ባሮክ | ፮ 14<br>ሰሎሜ ቅድስት፡<br>የደብረ ሊባኖሷ<br>ኢትዮጵያዊት። | ፯ 15 |
| ፰ 16 | ፱ ዕሌኒ 17<br>ንግሥት፡<br>የመሲሕ<br>ኢየሱስን<br>መስቀል<br>አስቆፍራ<br>አስገኘች። | ፲ 18<br>አናንያ፥<br>አዛርያና<br>ሚሳኤል፡<br>በሃይማኖታቸው<br>ጽናት ከባቢሎን<br>እሳት ዳኑ። | ፲፩ 19<br>ያሬድ፡ ኢትዮጵያዊው<br>ማሕሌታይ ካህን።<br>ገዳማዊ አሴር፡ የባሌ<br>መምህር። | ፲፪ 20<br>ዕርገት<br>አጼ እስክንድር፡<br>የእስላምን ወራሪ<br>ጦር ሲከላከል፡<br>ሰማዕትነትን፡<br>በወጣትነቱ የተቀበለ።<br>ዮሓንስ አፈወርቅ | ፲፫ 21<br>የደብረ-ሊባኖስ<br>ገዳም አባሎች፡<br>በ፲፱፻፳፱ ዓ.ም.<br>በፋሺስት ጣልያን<br>ጦር ተሠዉ። | ፲፬ 22 |
| ፲፭ 23<br>ናትናኤል፡<br>ከ፲፪ቱ<br>ሓዋርያት<br>፩ዱ። | ፲፮ 24 | ፲፯ 25 | ፲፰ 26 | ፲፱ 27 | ፳ ቅዱስ አጼ 28<br>ካሌብ ወደ<br>ናግራን (የመን)<br>ግዛቱ፡ በመርከብ<br>ዘምቶ፡ የአይሁድን<br>አሠቃቂ ወረራ<br>ድል አደረገ። | ፳፩ 29<br>የደርግ፡<br>የክህደትና<br>የዓመፅ አገዛዝ<br>በ፲፱፻፹፫<br>ዓ.ም.<br>ተወገደ። |
| ፳፪ 30<br>በዓለ<br>መንፈስ<br>ቅዱስ<br>(በዓለ<br>ኀምሳ) | ፳፫ 31<br>የሓዋርያት<br>ጾም<br>መግቢያ | ፳፬ 1<br>ዕንባቆም<br>ነቢይ። | ፳፭ የጾመ-ድኅነት 2<br>(የረቡዕና ዓርብ<br>ጾም) መነሻ።<br>ቅድስት ሰሎሜ፡<br>በሕፃኑ ኢየሱስና<br>በቅድስት ድንግል<br>እናቱ ስደት፡<br>ያልተለየች። | ፳፮ 3<br>ቶማስ፡<br>ከ፲፪ቱ<br>ሓዋርያት<br>፩ዱ። | ፳፯ 4<br>በ፲፱፻፹፫ዓ.ም.<br>ያዲስ አበባ ሕዝብ<br>ከተቀጣጠሉት የጦር<br>መሣሪያ ግምጃ<br>ቤቶች፡ የዕልቂት<br>እሳት ገሞራነት፡<br>በቅዱሱ ኪዳን፡<br>የከለላ ኃይል ዳነ። | ፳፰ 5 |
| ፳፱ 6<br>ገዳማዊ አፍጼ<br>እና ገዳማዊ<br>ጉባ፡ ከ፱ኙ<br>ቅዱሳን ፪ቱ። | ፴ 7 | ማስታወሻ፡- | | | | |

ሰላማችን ኢየሱስ መሲሕ፡ወደመቅደስ ወጥቶ ሲያስተምር፡ ሊገድሉት ለሚፈልጉት አይሁድ፡ "**ኢትፍትሑ፡ በአድልዎ ገጽ! አላ፡ ፍትሐ-ጽድቅ ፍትሑ!** ቅን ፍርድን ፍረዱ እንጂ፡ **መልክን አይታችሁ** አትፍረዱ!" አላቸው። ለምን እንዲህ አላቸው? "መልክን አይታችሁ አትፍረዱ!" የሚለው የጌታ ቃል፡ ቀድሞ፡ በሙሴ ላይ የተነሣሣባቸው ቅንዓት የተከሠተው፡ በኢትዮጵያዊት ሚስቱ፡ በሲጳራ ምክንያት እንደነበረ ኹሉ፡ አኹን ደግሞ፡ በእርሱ፡ በኢየሱስ መሲሕ ኢትዮጵያዊነት ላይ የተቀጣጠለ መኾኑን ሲያመለክታቸው እንደኾነ፡ ማስተዋል ነው። "'**አኮ ከመ ደቂቀ ኢትዮጵያ አንትሙ በኀቤየ፡ ደቂቀ እስራኤል!**' **ይቤ እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ ይመልክ ስሙ።** ስሙ፡ 'ኹሉን የሚገዛ' የኾነ እግዚአብሔር፡ ‹የእስራኤል ልጆች! እናንተ፡ በእኔ ዘንድ፡ እንደኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁም።›አለ።" ሲል፡ ነቢዩ አሞጽ የተናገራቸውን ቃላት፡ በዚያን ጊዜም፡ አይሁድ አላስተዋሏቸውም። (ዮሓ. ፯፥ ፲፬-፳፬። ዘኁል. ፲፪፥ ፩-፲፮። አሞ. ፱፥ ፯።)

| የግንቦት ወር ምንባብ፡- | መጻሕፍተ አስቴር፥ ምሳሌ እና መክብብ። |
|---|---|

# ፳፻፲፱ (፳፻፲፱) ዓመተ ምሕረት ወርኀ ሰኔ ዘመነ ሉቃስ ብሥራታዊ [ወንጌላዊ]

2019 Era of Mercy, Month of Seney (June-July, 2027), Year of Luke the Evangelist

| እሑድ<br>ሰንበት ዝልፍት<br>Sunday | ሰኞ<br>Monday | ማግሰኞ<br>Tuesday | ረቡዕ<br>Wednesday | ሓሙስ<br>Thursday | ዓርብ<br>Friday | ሰንበት<br>Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ማስታወሻ፡- | | ፩ 8<br>ወንድሞቹ<br>የሸጡት የያዕቆብ<br>ልጅ ዮሴፍና፡<br>ኢትዮጵያዊት<br>ሚስቱ አስናት። | ፪ 9 | ፫ 10 | ፬ 11 | ፭ 12 |
| ፮ በ፲፱፻፳፱ ዓ.ም. 13<br>በፋሺስት ጣልያን<br>የታጠቀ፣<br>የተመራም፡ የራያ<br>እስላም፡ የሸዋ ቆላ<br>ኢትዮጵያውያንን፡<br>በሰለባ ጭምር ፈጀ። | ፯ 14 | ፰ 15 | ፱ 16<br>ሳሙኤል ነቢይ። | ፲ 17 | ፲፩ 18 | ፲፪ 19<br>ቅዱስ<br>ሚካኤል<br>ሊቀ-መላእክት<br>አጼ<br>ላልይበላል |
| ፲፫ 20 | ፲፬ 21 | ፲፭ 22 | ፲፮ 23 | ፲፯ 24<br>ገዳማዊ ገሪማ<br>ከ፱ኙ ቅዱሳን<br>፩ዱ። | ፲፰ 25 | ፲፱ 26 |
| ፳ ሕንጸታ፡ 27<br>በአዳምና ሔዋን ኪዳነ<br>ሰብሳብ፡ በኢትዮጵያ<br>የተመሠረተችው፡<br>የእግዚአብሔር<br>መንግሥት፡ በድንግል<br>ማርያም እና በኢየሱስ<br>መሲሕ ኪዳነ-<br>ምሕረት: በኢየሩሳሌም<br>ተገለጠች።<br>ኤልሳዕ ነቢይ። | ፳፩ 28<br>በቅዱሱ ኪዳን<br>ላይ ክህደትና<br>ዓመፅ<br>የፈጸመውን<br>የኢትዮጵያ<br>ትውልድ ሊቀጣ<br>የተላከው ደርግ፡<br>በ፲፱፻፷፮ ዓ.ም.<br>ተቋቋመ። | ፳፪ 29 | ፳፫ 30<br>ሰሎሞን ንጉሥ፡<br>የምኒልክ አባት። | ፳፬ 1<br>ሙሴ<br>(ጸሊም)<br>ኢትዮጵያዊ | ፳፭ 2<br>ያስቆሮቱ<br>ያይደለ<br>ሓዋርያው<br>ይሁዳ።<br>የጸደይ<br>(የበልግ)<br>ወራት<br>ማብቂያ | ፳፮ 3<br>ኢያሱ<br>ወልደ-ነዌ።<br>የክረምት<br>(የዝናም)<br>ወራት<br>መግቢያ። |
| ፳፯ 4 | ፳፰ 5 | ፳፱ 6<br>ቀዳማዊ አጼ<br>ቴዎድሮስ<br>በ፲፪፻፬ ዓ.ም.<br>የተቀባው ስመ<br>ጥሩው ጻድቅ። | ፴ የላስታ 7<br>ላልይበላል [ላሊበላ]<br>አብያተ ክርስቲያን<br>በ፲፭፻፳፭ ዓ.ም.<br>በአሕመድ ግራኝ ጦር<br>ተበዘበዙ። | ማስታወሻ፡- | | |

"ወነበበ መልአከ-እግዚአብሔር፡ ለፊልጶስ፤ ወይቤሎ፡- 'ተንሥእ! ወሑር፡ ጊዜ ቀትር፣ ፍኖተ በድው፡ ዘያወርድ፡ እምኢየሩሳሌም፡ ለጋዛ!' ወተንሥአ፤ ወሖረ፤ ወረከበ፡ ብእሴ፡ እምሰብአ ኢትዮጵያ፣ ኀፅዋ ለሕንደኬ፡ ንግሥተ-ኢትዮጵያ፥ ወመጋቢሃ ውእቱ፡ ላዕለ ኵሉ መዛግብቲሃ። ወሖረ ኢየሩሳሌም ይስግድ። ወእንዘ ይገብእ፡ ነበረ ዲበ ሠረገላሁ፤ ወያነብብ፡ መጽሓፈ ኢሳይያስ ነቢይ። ወይቤሎ መንፈስ ቅዱስ ለፊልጶስ።- 'ሑር! ትልዎ፡ ለዝ ሠረገላ!' ...ወይቤሎ ኅፅው፥ ...ወአስተብቍዖ ለፊልጶስ፡ ከመ ይዕርግ፥ ወይንበር ኀቡረ ምስሌሁ። የእግዚአብሔር መልአክ፡ ፊልጶስን፡ 'በቀትር ጊዜ ተነሥተህ፡ ከኢየሩሳሌም፡ ወደጋዛ ወደሚያወርደው፡ የምድረ-በዳ መንገድ ኺድ!' አለው። ተነሥቶም ኼደ። እነሆም፡ ከኢትዮጵያ ሰዎች የኾነ አንድ ሰውን አገኘ። እርሱም፡ 'ሕንደኬ' የተባለች የኢትዮጵያ ንግሥት ጃንደረባዋ የኾነ፥ በሀብቷም ላይ ኹሉ የሠለጠነ፡ በኾሮንዴ ነው፤ ወደኢየሩሳሌም መጥቶ፡ ከተሳለመ በኋላ፡ በሠረገላው ተቀምጦ ሲመለስ፡ የነቢዩን የኢሳይያስን መጽሓፍ እያነበበ ነበረ። መንፈስ ቅዱስም፡ ፊልጶስን፡- 'ኺድ! ይህን ሠረገላ ተከተል!' አለው። ...ጃንደረባውም፡ ፊልጶስን አናገረው፤ ወደሠረገላው ወጥቶ፡ ከእርሱ ጋር ዓብሮት እንዲቀመጥም ለመነው።" የዐዲስ ኪዳኑ አቤሜሌክ የኾነው ጃንደረባም፡ ወዲያው፡ "ኢየሱስ መሲሕ፡ የእግዚአብሔር ልጅ እንደኾነ አምናለሁ!" ስላለ፡ ፊልጶስ፡ እዚያው አጠመቀው። ከጥምቀቱም በኋላ፡ ጃንደረባው አቤሜሌክ፡ በተደረገለት፡ መለኮታዊ የቸርነት ሥራ፥ በተቀዳጀውም፡ ዘለዓለማዊ፡ የመንፈስ ቅዱስ ብፅዕና፡ በደስታ እጅግ ተመሥጦ ስለነበረ፡ ፊልጶስ፡ ከአጠገቡ፡ በመንፈስ ቅዱስ ተነጥቆ የመወሰዱን ተአምር ሳያስተውል፡ ዝም ብሎ፡ የሠረገላ መንገዱን ቀጠለ።" (የሓዋ. ፰፥ ፳፮-፴፱።)

| የሰኔ ወር ምንባብ፡- | የሓዋርያት ሥራ እና ንኡሳኑ መልእክታት። |
|---|---|

# ፪ሺ፲፱ (፳፻፲፱) ዓመተ ምሕረት ወርኀ ሓምሌ ዘመነ ሉቃስ ብሥራታዊ [ወንጌላዊ]

2019 Era of Mercy, Month of Hamley (July-Aug., 2027), Year of Luke the Evangelist

| እሑድ<br>ሰንበት ዝልፍት<br>Sunday | ሰኞ<br>Monday | ማግሰኞ<br>Tuesday | ረቡዕ<br>Wednesday | ሓሙስ<br>Thursday | ዓርብ<br>Friday | ሰንበት<br>Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| **ማስታወሻ:-** | | | | ፩ 8 | ፪ 9<br>**ታዴዎስ፡**<br>**ከ፲፪ቱ**<br>**ሓዋርያት**<br>**፩ዱ።** | ፫ የእግዚአብሔር10<br>መንግሥት ኢትዮጵያ:<br>መልእክተኛ:ኪዳናዊው<br>የአኵስም ጽዮን ንቡረ-<br>እድ (ቄስ) ኤርምያስ<br>ከበደ ወልደ ኢየሱስ<br>ዓባይነሽ፡ ልደት። |
| ፬ 11<br>**የጾመ**<br>**ሓዋርያት**<br>**ማብቂያ።** | ፭ 12<br>**በዓለ ቅዱሳን**<br>**ሓዋርያት፡**<br>**ጴጥሮስ**<br>**ወጳውሎስ።** | ፮ 13<br>**ዕርገተ**<br>**እዝራ።** | ፯ 14<br>**ሥሉስ ቅዱስ**<br>**በአብርሃም ቤት**<br>**የተገኙበት።**<br>በ፲፱፻፳፱ዓ.ም.<br>በፋሺስት ጣልያን<br>ጦር በሰማዕትነት<br>የተሠዉት ፳፭ቱ<br>የደብረ-ሊባኖስ<br>ገዳም አባላት። | ፰ 15 | ፱ 16 | ፲ 17 |
| ፲፩ 18 | ፲፪ 19 | ፲፫ 20 | ፲፬ 21 | ፲፭ 22<br>**ኤፍሬም፡**<br>የውዳሴ ማርያም<br>ደራሲ። | ፲፮ 23 | ፲፯ 24<br>**ነቢዩ ዮናስ፡**<br>**ነነዌ ገባ።** |
| ፲፰ 25<br>**ያዕቆብ፡**<br>በኢየሩሳሌም፡<br>የቤተ-ክርስቲያን<br>የመጀመሪያው<br>ሊቀ-ካህናትና<br>ሰማዕት።<br>የኢትዮጵያ ልጆች<br>**ጦቢያና ጦቢት** | ፲፱ 26<br>**ቅዱስ ገብርኤል**<br>**ሊቀ-መላእክት፡**<br>**ሕፃኑን ሰማዕት**<br>**ቅዱስ ቂርቆስንና**<br>**እናቱን ቅድስት**<br>**ኢየሉጣን ተጥለውበት**<br>**ከሚነድድባቸው እሳት**<br>**አዳነ።** | ፳ 27 | ፳፩ 28<br>**አጼ ሠርፀ-**<br>**ድንግል**<br>**ሃይማኖታዊው**<br>**ተጋዳይ።** | ፳፪ 29<br>**ቅዱስ**<br>**ዑራኤል**<br>**ሊቀ-**<br>**መላእክት** | ፳፫ 30<br>**ቅዱስ ጴጥሮስ**<br>**ኢትዮጵያዊው**<br>**ገዳማዊ ሰማዕት፡**<br>**በ፲፱፻፳፰ዓ.ም.**<br>**በፋሺስት**<br>**የጣልያን ጦር**<br>**በግፍ ተገደለ።** | ፳፬ **የደብረ** 31<br>**ሊባኖስ ገዳም**<br>በ፲፭፻፳፫ ዓ.ም.<br>በአሕመድ ግራኝ<br>ተቃጠለ። ከገዳሙ<br>አባሎች መካከል፡<br>እየራሳቸውን፡ ለእሳቱ፡<br>በሰማዕትነት ማገዱ። |
| ፳፭ 1<br>**ገዳማዊ**<br>**ሕፃን-ሞአ**<br>**ኢትዮጵያዊ።** | ፳፮ 2<br>**ጻድቅ ዮሴፍ**<br>**ኢትዮጵያዊ፡ ሕፃኑን**<br>**ኢየሱስንና እናቱን**<br>**ድንግል ማርያምን**<br>**ለማገልገል በመብቃቱ**<br>**በፈጣሪ የተመረጠ**<br>**ጻንደረባ።** | ፳፯ 3 | ፳፰ 4 | ፳፱ 5 | ፴ 6<br>**ማርያም**<br>**ክብራ**<br>(እቴጌ ናዖድ<br>ሞገሳ) የአጼ<br>ናዖድ ሚስት | **ማስታወሻ:-** |

"ወአንጐርጐሩ አይሁድ በእንቲአሁ፣ እስመ ይቤሎሙ፡- 'አነ ውእቱ፡ ኅብስተ-ሕይወት፣ ዘወረደ እምሰማይ!' ወይቤሉ፡- 'እፎ ይክል ዝንቱ፡ የሀበነ ሥጋሁ ንብላዕ?' እንግዴህ፡ ኢየሱስ፡ 'ከሰማይ የወረደ እንጀራ፡ እኔ ነኝ!' ስላላቸው፡ አይሁድ፡ ስለእርሱ አንጐራጐሩ፤ 'እንዴትስ፡ ይህ ሰው፡ ሥጋውን እንበላ ዘንድ ሊሰጠን ይችላል?' አሉም።" ከዚህ የተነሣ፡ "ወብዙኃን፡ እምአርዳኢሁ፡ እለ ሰምዑ፡ ወይቤሉ፡ 'ዕፁብ ዝንቱ ነገር! ወመኑ ይክል ሰሚዖቶ? ...ወገብኡ ድኅሬሆሙ፤ ወኢሖሩ እንከ ምስሌሁ።' ከደቀ-መዛሙርቱ መካከል ሳይቀር፡ ይህን የሰሙ፡ ብዙዎች፡ 'ይህ፡ የሚያስጨንቅ ንግግር ነው! ማን ሊሰማው ይችላል?' ብለው፡ እርሱን መከተልን ትተው፡ ወደኋላቸው ተመለሱ።" በዚህ ጊዜ፡ ሰላማችን ኢየሱስ መሲሕ፡ "አማን አማን እብለክሙ! እመ ኢበላዕክሙ ሥጋሁ፡ ለወልደ ዕጓለ-እመሕያው፣ ወኢሰተይክሙ ደሞ፡ አልብክሙ ሕይወት ላዕሌክሙ። ዘበልዐ ሥጋየ፥ ወሰትየ ደምየ፡ ቦ ሕይወት ዘለዓለም። ወአነ አነሥኦ፡ በደኃሪት ዕለት። እውነት እውነት እላችኋለሁ! የማርያምን ልጅ ሥጋ ካልበላችሁ፥ ደሙንም ካልጠጣችሁ፡ በእየራሳችሁ፡ ሕይወት የላችሁም። ሥጋዬን፡ የበላ፤ ደሜንም፡ የጠጣ፡ የዘለዓለም ሕይወት አለው። እኔም፡ በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ።" ሲል፡ ሊድን ለሚፈልግ፡ ለዓለሙ ሰብአዊ ፍጡር ኹሉ፡ የመጨረሻ ዓዋጅ የኾነውን፡ የእግዚአብሔርን እውነት፡ ገልጦና አስረግጦ ተናገረ። (ዮሓ.፮፥ ፵፩-፷፮።)

| የሓምሌ ወር ምንባብ፡- | ደቂቀ ነቢያት እና የዮሓንስ ብሥራት [ወንጌል]። |
|---|---|

# ፪ሺ፲፱ (፳፻፲፱) ዓመተ ምሕረት ወርኀ ነሐሴ ዘመነ ሉቃስ ብሥራታዊ [ወንጌላዊ]

2019 Era of Mercy, Month of Nehassey (Aug.-Sept., 2027), Year of Luke the Evangelist

| እሑድ<br>ሰንበት ዝልፍት<br>Sunday | ሰኞ<br>Monday | ማግሰኞ<br>Tuesday | ረቡዕ<br>Wednesday | ሓሙስ<br>Thursday | ዓርብ<br>Friday | ሰንበት<br>Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| **ማስታወሻ፡-** | | | | | | ፩ 7<br>**የፍልሰታ ለማርያም ጾምና ሱባዔ መግቢያ።**<br>ኢየሱስን የገነዙት ዮሴፍና ኒቆዲሞስ። |
| ፪ 8 | ፫ 9 | ፬ 10 | ፭ 11<br>**ገዳማዊ ፊልጶስ፡**<br>ዘደብረ-ቢዘን | ፮ **ማርያም** 12<br>**መግደላዊት፡**<br>የመሲሕን ትንሣኤ ቀድማ አይታ አበሠረች። | ፯አጼ ናዖድ13<br>የመልክዓ ማርያምና የመልክዓ ኢየሱስ ደራሲ። | ፰ 14 |
| ፱ 15 | ፲ 16 | ፲፩ 17 | ፲፪ 18 | ፲፫ **ቡሔ** 19<br>**ደብረ-ታቦር፡**<br>ጌታ፡በግርማ መለኮቱ ታየ። | ፲፬ 20<br>የፍልሰታ ለማርያም ሱባዔ ማብቂያ። | ፲፭ 21<br>የፍልሰታ ለማርያም ጾም ማብቂያ። |
| ፲፮ 22<br>**የድንግል ማርያም በዓለ ፍልሰታ (ፍልሰተ-ትንሣኤዋ)** | ፲፯ 23 | ፲፰ 24<br>**አዝማች አዳሉ፡**<br>በአሕመድ ግራኝ ወረራ የተሠዋ። | ፲፱ 25 | ፳ 26 | ፳፩ 27 | ፳፪ 28 |
| ፳፫ 29<br>**ገዳማዊ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ ኢትዮጵያዊው**<br>የመዓዛ ቅዳሴና የሰዓታት፥የሌሎችም ጸሎታት ደራሲ። | ፳፬ **እጨጌ** 30<br>**ተክለ-ሃይማኖት፤**<br>በ፲፪ኛው ፻ ዓመት፡ ኢትዮጵያዊው ሥርዓተ መንግሥት ወደሰሎሞናዊው አገዛዝ እንዲመለስ ያስማማ።<br>**ክርስቶስ ሠምራ፡ ለኢትዮጵያዊነት** አብነት። | ፳፭ 31 | ፳፮ 1 | ፳፯ 2<br>**አጼ ዓምደ ጽዮን፡ ስለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ተጋደለ።** | ፳፰ 3<br>**አብርሃም፥ ይስሓቅና ያዕቆብ።** | ፳፱ **ንዋየ-** 4<br>**ክርስቶስ** (አለቃ ዘካርያስ)፡ እስላም ሣለ እስላሞችን በቁርዓናቸው የረታና ብዙዎቹን ያስጠመቀ ኢትዮጵያዊ ሓዋርያ ለኢትዮጵያዊነት፡ አብነትና ድልድይ የኾነ። |
| ፴ ኢትዮጵያዊው 5<br>**መልከ-ጼዴቅ፡**<br>እሱም ቅዱሱን ኪዳን ከኖኅ የተረከበው፡ የፊተኛው አብርሃምን በባረከው በማእከላዊው አማካይነት፡ ለመጨረሻውና ለአማናዊው መልከ ጼዴቅ ኢየሱስመሲሕ ቀዳሚአርአያ የኾነው | **ጳ ጉ ሜ** | | | | | |
| | ፩ 6<br>**የንስሓ ጾም መግቢያ።** | ፪ 7 | ፫ 8<br>**ቅዱስ ሩፋኤል፡ ሊቀ መላእክት**<br>**አጼ ዘርዓ ያዕቆብ** | ፬ 9<br>**የቅዱሳንና የቅዱሳት ኹሉ ዝክር።** | ፭ 10<br>**ዓሞጽ ነቢይ።** | ፮ 11<br>**የንስሓ ጾም ማብቂያ።** |

መልአኩ፡ ቅዱስ ገብርኤል፡ እግዝእተብሔር እም የተዋሓደቻትን፡ ድንግል ማርያምን፡ "**ተፈሥሒ ፍሥሕት፡አ ምልዕተ-ጸጋ፡ እግዚአብሔር ምስሌኪ! ቡርክት አንቲ እምአንስት!** ከሴቶች ኹሉ ተለይተሽ የተባረክሽው፥ እግዚአብሔርም፡ ካንቺ ጋራ የኾነው፡ አንቺ፡ ጸጋን የተመላሽ፡ ደስተኛዪቱ ሆይ! ደስ ይበልሽ!" አላት። መንፈስ ቅዱስ የመላባት ኤልሣቤጥም፡ "**ቡርክት አንቲ እምአንስት! ወቡሩክ ፍሬ ከርሥኪ**! ከሴቶች ኹሉ ተለይተሽ፡ አንቺ የተባረክሽ ነሽ! የማሕፀንሽም ፍሬ፡ የተባረከ ነው!" አለቻት። ራሷ ቅድስት ድንግል ማርያምም፡ "**ታዐብዮ ነፍስየ ለእግዚአብሔር! ወትትሐሠይ መንፈስየ፡ በአምላኪየ፥ ወመድኃኒየ! እስመ ርእየ ሕማማ ለአመቱ! ናሁ እምይእዜሰ፡ ያስተበፅዑኒ፡ ኵሉ ትውልድ!እስመ ገብረ ሊተ፤ ኃይለ ዐቢያተ!** ነፍሴ፡ እግዚአብሔርን፡ ታልቀዋለች! መንፈሴም፡ በአምላኬና በመድኃኒቴ፡ እጅግ ደስ ይላታል! የአገልጋዩን መከራ አይቷልና! እነሆ፡ ከዛሬ ጀምሮ፡ ትውልድ ኹሉ፡ ያመሰግኑኛል! እርሱ፡ ለእኔና በእኔ፡ ታላላቅ ተአምራትን አድርጓልና። (ሉቃ. ፩፥ ፳፮-፶።)

| | |
|---|---|
| የነሓሴ እና የጳጉሜ ወራት ምንባባት፡- | መጽሓፈ ጦቢት እና የሉቃስ ብሥራት [ወንጌል]። |

† † †